የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፹፬
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.84.
ADDIS ABABA 20th October, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፯/፪ሺ፲፫ ዓ.ም

ለአሰላ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዳንስኬ ባንክ ኤ.ስ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ………………………………………………ገጽ ፲፪ሺ፰፻፸፯

## Content

Proclamation No.1227/2020

Danske Bank A/S Loan Agreement for financing Asela Wind Power Project Ratification Proclamation............................................Page 12,877

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፯/፪ሺ፲፫

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዳንስኬ ባንክ ኤ.ስ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአሰላ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፩፻፲፯ ሚሊዮን ፫፻ ሺ.ህ ዩሮ (አንድ መቶ አስራ ሰባት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺ.ህ ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዳንስኬ ባንክ ኤ.ስ መካከል ሰኔ ፲ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መስከረም ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ባካሄደው ፬ኛ አስቸኳይ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1227/2020

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE DANSKE BANK A/S

WHEREAS, the Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Danske Bank A/S stipulating that the Danske Bank A/S provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 117,300,000 Euro (One Hundred Seventeen Million Three Hundred Thousand Euro) for financing Asela Wind Power Construction Project, was signed in Addis Ababa on 17th day of June, 2020;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its 4th urgent session held on the 22nd day of September, 2020

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለአሰላ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዳንስኬ ባንክ ኤ.ስ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳፯/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዳንስኬ ባንክ ኤ.ስ መካከል ሰኔ ፲ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ፀድቋል፡፡

፫. **የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፲፯ ሚሊዮን ፫፻ ሺህ ዩሮ (አንድ መቶ አስራ ሰባት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺህ ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፲ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Danske Bank A/S Loan Agreement for financing Asela Wind Power Project Ratification Proclamation No. 1227/2020".

2. **Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement signed in Addis Ababa on 17th day of June 2020 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Danske Bank A/S is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 117,300,000 Euro (One Hundred Seventeen Million Three Hundred Thousand Euro) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the *Federal Negarit Gazettee.*

**Done at Addis Ababa, on this 20th day of October, 2020**

**SAHILEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**